ዜማ ይወጽእ እምያሬድ ዘኢትዮጵያ

ወቃለ እግዚአብሔር እምኢሩሳሌም

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

እኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ልጆች በቤተ ክርስቲያ ውስጥ ሥርዓተ አምልኮ የሚፈጸምባቸውን ዜማዎች አሁን ዘመኑ ባፈራው ጥበብ ወደ ድምፀ መዛግብት ቢቀየር ለብዙ ነገር እጅግ ጠቃሚ እንደሚሆን ስለአሳመነን ከውሳኔ ላይ አደረስን ፡

ይኽም ሥራ ከውጭ ሀገር የኑሮ ክብደትና የጊዜ ዕጥረት ጋር ብዙ ድካም የጠየቀና ወደፊትም የሚጠይቅ ቢሆንም በእግዚአብሔር አጋዥነት እየተዘጋጀ ነው ይኽም ዝግጅት ለማን እንደሚጠቅምና እንደሚያገለግል ለመግለጽም ካስፈለገ ዋና ዋና ምክንያቶቹም እነሆ ፡

፩ኛ - በሀገር ቤት ያሉ የቆሎ ተማሪዎች ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ እጅግ እየቀነሰ በመሄዱ .

፪ኛ - ይኽም አባቶቻችን ሊቃውንት በብዙ ድካም ያቆዩልንን በገንዘብ ሊገዛና ሊተመን የማይቻል ታላቅና ውድ ቅርስ ድንገት እንዳይጠፋ . ድካማቸውም ሁሉ ከንቱ ሆኖ እንዳይቀርና ብሎም ለዘመነ ዘመናት ቀጣይ ሆኖ እንዲኖር ለማረጋገጥ.

፫ኛ - በሀገር ቤት ያሉትን የመምህራን ድካም ለመቀነስ

፬ኛ - ተማሪዎች በቅፀላ የሚያባክኑትን ጊዜ ለመቆጠብ

፭ኛ - ትምህርቱን ጀምረው ላቋረጡና እንዲሁም ተምረው ለብዙ ዘመናት በሥራ ምክንያት ተለይተው ለቆዩ ማስታወሻ ይሆን ዘንድ .

፮ኛ - በውጭ ሀገር የሚኖሩ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ችግር ሲገጥማቸው በውጭ ተጠያቂ መምህራን ስለማያገኙ የካህናትን ችግር ለማስወገድና ብሎም ይኽንን በቀላሉ እያጠኑ ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግሉ ነው .

ይኽ ዝግጅት ለምን እንደተዘጋጀና ለማን እንደሚያገለግል ጥቂት ካልን በኋላ ለዚህም አገልግሎት የተዘጋጁትን ከዚኽ እንደሚከተለው ልንገልጽ እንወዳለን .

፩ኛ - ድጓ

፪ኛ - ጾመ ድጓ

፫ኛ - ምዕራፍ

፬ኛ - ዝማሬ

፭ኛ - መዋሥዕት

፮ኛ - አቋቋም ዘወንበር ዘክብረ በዓል ዘበዓታ

፯ኛ - አቋቋም ዘወንበር ዘወርኃ በዓል ዘበዓታ

፰ኛ - አቋቋም ዘተክሌ ዘወንበር ዘክብረ በዓል

፱ኛ - አቋቋም ዘተክሌ ዘወንበር ዘወርኃ በዓል

፲ኛ - አቋቋም ዘመዋሥዕት

፲፩ኛ - አቋቋም ዘቅንዋት

፲፪ኛ - አቋቋም ዘወርኃ በዓላት በወንበር የማይነገሩ

፲፫ኛ - መዝሙር ዘበዓታ ወዘተክሌ - አቋቋም

፲፬ኛ - የተክሌ ዝማሜ

፲፭ኛ - መዝገብ ቅዳሴ ዘደብረ ዓባይ

፲፮ኛ - የዓመቱ ምስማክ

፲፯ኛ - ሰዓታት ዘደብረ ዓባይ

፲፰ኛ - ወረብና የአንገርጋሪ ንሽ ናቸው . እነዚህ ሁሉ ተቀርፀው በእጃችን የሚገኙ ሲሆን ሁሉም ተዘጋጅተው ሲያበቁ ቀስ በቀስ በኢንተርኔት የሚለቀቁ መሆናቸውን ልንገልጽ እንወዳለን ፡

ምስጋና . ይኽንንም ዕቅድ ወደ ተግባር ለመተርጎም እንዲቻል በሃሣብም ሆነ በጥሪት የረዱንን

፩ኛ - ብፁዕ አቡነ ኤጲፋንዮስ የምዕራብ ሸዋ ሊቀ ጳጳስ

፪ኛ - መጋቢ አዕላፍ ክቡር ጥላሁን በጎንደር በአታ የአቋቋም ምስክር ት/ቤት መምህር

፫ኛ - መጋቢ ትፍሥሕት ዘምሮ አበራ

፬ኛ - ዲያቆን ግርማ ደምሴ

5ኛ - መልአከ ገነት ማንደፍሮ እንግዳሰው

6ኛ - መልአከ ምሕረት አስፋው ከልብ እናመሰግናለን

በተለይም ደግሞ ደከመን ሰለቸን ሳይሉ ይኸን ቃለ እግዚአብሔር በብዙ ድካም የቀረጹልንን

፩ኛ - መምህር ቀለሙ እንዳለው . የድጓ ፤ የአቋቋም ፤ የዝማሬ መዋሥእትና የመዝገብ ቅዳሴ መምህር ዘጎጃም .

፪ኛ - መምህር አስተርአየ ካሣየ የአቋቋም መምህር - ዘላስታ ላሊበላ

፫ኛ - መምህር ምክሩ የድጓ መምህር - ዘባሕር ዳር

፬ኛ - መምህር በቃሉ የአቋቋም መምህር - ዘደብረ ምጥማቅ

፭ኛ - መምህር ኤርምያስ ብርቅነህ የአቋቋም መምህር - ዘደብረ ሊባኖስ

፮ኛ - መምህር ልዑለ ቃል ኃይልየ የአቋቋም መምህር - ዘደብረ ሊባኖስ

፯ኛ - መምህር ሲሳይ ታደሰ የአቋቋም መምህር - ዘደብረ ሊባኖስ

፰ኛ - መምህር አስተርአየ ደሴ የአቋቋም መምህር - ዘደብረ ሊባኖስ

የሰዎችን የድካም ዋጋ የማያስቀር አምላከ አበው ዋጋቸውን ይክፈልልን . እንዲሁም ደግሞ በቅርብም ሆነ በሩቅ የሚገኙ ጓደኞቻችን በሃሣብ በጣም ስለአበረታቱን ከልብ እናመሰግናቸዋለን

ይኸ ሥራ መታሰቢያነቱ

፩ኛ - ለአባቶቻችን ለኢትዮጵያ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን

፪ኛ - ከሚበላውና ከሚጠጣው እየከፈለ እያበላና እያጠጣ ስንቅ ሆኖ ላስተማረን ለታላቁ ባለውለታ ለኢትዮጵያ ገበሬ ነው ፡

የአበው በረከት . የቅዱሳን መላእክትና የጻድቃን ሰማዕታት ተራዳኢነት . የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት የእግዚአብሔር ምሕረትና ቸርነት ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን .

አዘጋጆች

፩ኛ - ሊቀ ማዕምራን ቃለ አብ አዱኛ - ዘጎንደር

፪ኛ - ሊቀ ትጉሃን አፈ ወርቅ መንግሥቴ - ዘሸዋ

የተዘጋጀው - በኢየሩሳሌም

እስራኤል